**የሲዳማ በክልልነት የመደራጀት ሕዝበ ውሳኔ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በህገ መንግሥቱ እና በተለያየ ወቅት በጸደቁት የምርጫ ህጎች አማካኝነት የጠቅላላ፣ የአካባቢ፣ የድጋሚ፣ የማሟያ ምርጫዎች በተጨማሪ ሕዝበ ውሳኔዎችን ሲያከናውን ቆይቷል። ቦርዱ ከተመሠረተ አንስቶ ስድስት/6/ ሕዝበ ውሳኔዎችን አስፈጽሟል። አዲሱ የምርጫ እና የፓለቲካ ፓርቲዎች አዋጅ 1162/2011 አንቀጽ 11 የሕዝበ ውሳኔ የማስፈጸም ስልጣን የቦርዱ እንደሆነ ይደነግጋል።

**ሕዝበ ውሳኔ ህግ ማዕቀፍ፦**

**አንቀጽ 11 - 1162/2011**

፩/ ቦርዱ በህገ መንግሥቱ ወይም በሌሎች ህጎች መሠረት አግባብ ባለው አካል ሲወሰን የሕዝብን ፍላጎት ለመለካት ወይም ለመወሰን ድምፅ እንዲሰጥ ሕዝበ ውሳኔ የሚሰጥበትን ምርጫ ያዘጋጃል፡ ፡

፪/ ሕዝበ ውሳኔው እንዲካሄድ ከወሰነው አካል ጋር በመመካከር ቦርዱ ሕዝበ ውሳኔ ያስፈለገበትን ጉዳይ ለመለየት በሚያስችለው መልኩ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን በማደራጀት ሕዝበ ውሳኔውን ያከናውናል።

፫/ ቦርዱ በህገ መንግሥቱ ስልጣን ከተሰጠው አካል ጋር በመመካከር ድምፅ የሚሰጥበትን ቀን፥ በሕዝበ ውሳኔው በድምፅ ሰጪነት ለመሳተፍ ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች በድምፅ መስጫ ወረቀቱ ላይ የሚሠፍረው ለውሳኔ የቀረበው አማራጭ አጻጻፍ እና የሕዝበ ውሳኔውን አስመልክተው የሚደረጉ የቅስቀሳ ዓይነቶችን ይዘት ይወስናል።

፬/ ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

በዚሁ አዋጅ መሠረት ለሕዝበ ውሳኔ ድምፅ ሰጪነት የሚያስፈልጉት መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው።

**ድምፅ ሰጭነት ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች፦**

- ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሆነ/የሆነች፣
- በሲዳማ ዞን ስር በሚገኙ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ውስጥ ነዋሪ የሆነ/የሆነች፣
- በምዝገባው ዕለት ዕድሜው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ/የሆነች፣
- በቀበሌው 6 ወር የኖረ/የኖረች ናቸው፣
- የዝበ ውሳኔ ተመዝጋቢው በመደበኛነት ነዋሪ መሆኑን እና ማንነቱን የሚያሳይ ሰነድ በማቅረብ መመዝገብ ይችላል
- አስፈጻሚዎች የተመዝጋቢውን ነዋሪነት ማረጋገጥ አለባቸው።

**በድምፅ ሰጪነት ሊመዘገቡ የማይችሉ፦**

- ኢትዮጵያዊ ዜጋ ያልሆነ/ያልሆነች፣
- በምዝገባው ዕለት ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ/የሆነች እና በድምፅ መስጫ ጣቢያው ከ6 ወር በታች የኖሩ፣
- በአእምሮ ህመም ምክንያት የመወሰን አቅም የሌለው/የሌለት መሆኑ ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠበት/ የተረጋገጠባት ሰው፣

- የመምረጥ መብቱ በህግ ወይም አግባብ ባለው ህግ መሠረት በፍርድ ቤት ውሳኔ የተገደበበት/የተገደበባት ሰው ናቸው፡፡

**የሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ**

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በቁጥር ክም/አ/9/7092/2011 በቀን 12/3/2011 በተፃፈ ደብዳቤ መሠረት ሲዳማ በክልልነት የመደራጀት ጥያቄ በተመለከተ ቦርዱ ሕዝበ ውሳኔ እንዲካሄድለት ጠይቋል፡፡

ቦርዱም ይህንን ጥያቄ ተከትሎ የሕዝበ ውሳኔውን ለማከናወን የሚያስፈልጉ የተለያዩ ዝግጅቶችን በማድረግ የአፈፃፀም የድርጊት መርሀ ግብር በማዘጋጀት፣ የተለያዩ ባለድርሻ አካለትን በማሳተፍ ሕዝበ ውሳኔውን ኅዳር 10 ቀን 2012 ዓ.ም. በተሳካ ሁኔታ አከናውኗል፡፡

ኅዳር 10 ቀን 2012 ዓ.ም. የተከናወነው የድምፅ መስጠት ሂደት ሰላማዊ እና ጉልህ የሎጀስቲክስ ችግር ያልታየበት ሲሆን አንዳንድ ቦታዎች ላይ የመራጮች ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ሰልፎች ከመኖራቸው በስተቀር በታቀደበት ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ በእለቱ የቦርድ አመራር አባላት የመስክ ጉብኝቶችን ያካሄዱ ሲሆን የምርጫ ቆጠራውም በእለቱ ተጠናቆ በየምርጫ ጣቢያዎቹ ተለጥፏል፡፡ በእለቱ ከመራጮች የሚመጡ ጥቆማዎችንም መሠረት በማድረግ የተለያዩ እርምት እርምጃዎች ሲከናወኑ ውለዋል፡፡ ቦርዱም የሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ የመጨረሻ ውጤት በኅዳር 24 ቀን 2012 ዓ.ም. የሚከተለውንም ውጤት ለሕዝብ ይፋ አድርጓል፡፡

| የመረጃ ዓይነት | ቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|
| የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር | 2,304,577 | |
| ድምፅ የሰጡ መራጮች ቁጥር | 2,279,022 | 98.8911 % |
| ድምፅ ያልሰጡ መራጮች ቁጥር | 25,555 | 1.10888 % |
| ለሻፌታ (ለሲዳማ ክልልነት መደራጀት ድምፅ የሰጡ) መራጮች ቁጥር | 1,984,283 | 97.7% |
| ለጎጆ (በደቡብ ክልል ለመቆየት ድምፅ የሰጡ) መራጮች | 30,018 | 1.478 % |
| የተሰረዘ ድምፅ | 248,097 | |
| ዋጋ አልባ ድምፅ መስጫ ወረቀት | 16,624 | |

**የሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ ዝግጅት**

**ውይይት መድረኮች**

***የኢትዮጵያ*** *ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አስቀድሞ ባወጣው የሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ አፈጻጸም መርሀ ግብር መሠረት የተለያየ ኃላፊነት ያላቸው የህግ አስፈጻሚ እና የጸጥታ አካላት እና የቦርዱ የሥራ አመራር*

*አባላት የሕዝበ ውሳኔውን አፈጻጸም ሰላማዊነት ማረጋገጥ አስመልክቶ መስከረም 07 ቀን 2012 ዓ.ም. ውይይት አካሂደዋል።*

በውይይቱም የፌደራል ፓሊስ ተወካዮች፣ የደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ፓሊስ ኮሚሽን ተወካዮች፣ በክልሉ የተቋቋመው ኮማንድ ፖስት ኃላፊ፣ የሀዋሳ ከተማ ፓሊስ አዛዥ፣ የሲዳማ ዞን ፓሊስ ኃላፊ፣ የክልሉ የአስተዳደር እና ጸጥታ ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ ተገኝተው ሰፊ ውይይት ተደርጓል።

በመጨረሻም በሂደቱ (በሕዝበ ውሳኔው ዝግጅት፣ ድምፅ አሰጣጥ እና ድህረ ሕዝበ ውሳኔው) ሊያጋጥሙ የሚችሉ የጸጥታ ችግሮችን፣ መውሰድ ያለባቸው የመፍትሄ ተግባራትን እና ኃላፊነቱን የሚወስደውን አካል የሚያሳይ የሕዝበ ውሳኔ ፀጥታ እቅድ በስብሰባው ተሳታፊ በሆኑት የህግ አስፈጻሚዎች ተዘጋጅቶ መስከረም 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በሚደረገው የጋራ ስብሰባ ላይ እንዲቀርብ ከስምምነት ተደርሷል። መስከረም 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በጋራ ውይይት የተካሄደ ሲሆን ውይይቱ ላይም የጸጥታ እቅዱ ቀርቧል።

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሲዳማ ዞን ሕዝበ ውሳኔን አፈጻጸም አስመልክቶ ከክልልና ዞን ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሲዳማ ዞን ሕዝበ ውሳኔን አፈጻጸም አስመልክቶ የተለያዩ አካላት ጋር የሚደረጉ የተለያዩ ውይይቶችን እንደሚያከናውን ባስቀመጠው የድርጊት መርሃ ግብር መሠረት ነሐሴ 30 ቀን 2019 ዓ.ም. ከደቡብ ክልል ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ምክር ቤት ተወካዮች፣ የክልሉ አመራር አባላትና ከዞኑ ተወካዮች ጋር ውይይት አካሂዷል።

### ጊዜ ሰሌዳ

የሕዝብ ወሳኔውን የአፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው የክልሉ እና የዞን መስተዳደር አካላት እንዲደርስ ለሕዝብም ይፋ እንዲሆን አድርጓል። በዚህም መሠረት ለሕዝበ ውሳኔ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልገውን በጀት በክልሉ መንግሥት እንዲፈቀድ ተደርጓል። ሕዝበ ውሳኔው በሰላማዊ ሁኔታ ለማስፈፀም አስፈላጊ ሁኔታዎችን የክልሉ ምክር ቤት አስቀድሞ እንዲፈጽም በጠየቀው መሠረት የሕዝበ ውሳኔ የሲዳማ ዞን በክልልነት እንዲደራጅ የሚል ከሆነ በዞኑ ውስጥ የሚኖሩ ሌሎች ብሔረሰቦች መብት ጥበቃንና አዲስ በሚፈጠረው እና ነባሩ ክልል መኃከል የሚኖረውን የሃብት ክፍፍል የሚወሰንበት አስተዳደርና በህግ ማእቀፍ አውጥቶ አቅርቧል።

### ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች

በቅድመ ሕዝበ ውሳኔ ዝግጅት በቦርዱ ባለሞያዎች የመስክ ጥናት አካሂደው የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን መረጃ አደራጅተዋል።

በዚህም መሠረት ለሕዝበ ውሳኔው ማስፈጸሚያ 1692 ምርጫ ጣቢያዎች የተቋቋሙ ሲሆን ከድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ በኂላ ተጨማሪ **169** የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ተደራጅተዋል። የሕዝበ ወሳኔው አፈፃፀም ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ እንዲያስችል ከክልሉ፣ ከዞኑ፣ ከሀዋሳ ከተማ እንዲሁም የፌደራል የጸጥታ ተቋማት እና አስተዳደር ተቋማት የሕዝበ ውሳኔው ፀጥታ እቅድ አዘጋጅተው አቅርበዋል።

### የሕዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች

ሕዝበ ውሳኔውን በገለልተኝነትና በህግ መሠረት የሚያስፈፅሙ 6,843 አስፈፃሚዎችን ከአዲስ አበባ ከተማ እና ኦሮምያ ክልል አከባቢዎች በመመልመል በዞኑ ያሰማራ ሲሆን ሁሉም አስፈጻሚዎች ሕዝበ ውሳኔውን እንዴት እንደሚያስፈጽሙ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል።

ስልጠናውም ቀድመው የአሰልጣኞች ስልጠና በወሰዱ 20 አሰልጣኞች ለ5 ቀናት የተከናወነ ሲሆን ሁሉም አስፈጻሚዎች የታተመ የማስፈጸሚያ ማንዋል እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡

**የድምፅ መስጫ ቁሳቁሶች**

የድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ ከተጠናቀቀበት እስከ ድምፅ መስጫው ቀን ባሉት ጥቂት ቀናት ቦርዱ የድምፅ መስጫ ቁሳቁሶችን 3,000 (ሶስት ሺህ) የድምፅ መስጫ ሳጥኖች እና 2.5 ሚልዮን በላይ (መጠባበቂያን ጨምሮ) የድምፅ መስጫ ወረቀቶች እንዲሁም የተለያዩ ቅጾችን አሰራጭቷል፡፡

**የፀጥታና ደህንነት ሁኔታ**

ከቅድመ ሕዝበ ውሳኔ ዝግጅት እስከ ድህረ ሕዝበ ውሳኔ የነበረው የፀጥታና ደህንነት ሁኔታ በዚህ እቅድ መሠረት በጋራ ኮሚቴ በየጊዜው እየታየ ሰላማዊ ሕዝበ ውሳኔ ለማካሄድ ተችሏል፡፡

በሕዝበ ውሳኔው ሂደት ጸጥታ እና ደህንነት አስመልክቶ ቦርዱ ሂደቱን በሚመራበት ወቅት የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም መረጃ በመሰብሰብ፣ በሀዋሳ ከተማ እንዲሁም በሌሎች ወረዳዎች የሚገኙ ምርጫ ጣቢያዎች የመስክ ጉብኝት አድርጓል፡፡

ከአስተዳደር ወሰን ጋር በተያያዘ እና ቀድሞ ግጭት በነበረባቸው የተወሰኑ ቀበሌዎች ከማህበረሰብ ክፍሎች የቀረቡ አቤቱታዎችን በማዳመጥ የቦርድ አመራር አባላት በቦታው በመገኘት የመስክ ቅኝቶችን አድርገው ከቀበሌ አስተዳደሮች ጋርም ውይይት አድርገዋል፡፡ ከውይይቱም በተጨማሪ የሲዳማ ዞን እና የደቡብ ክልል የጸጥታ አካላት፣ የፌደራል ፓሊስ እንዲሁም የመከላከያ ሰራዊትን ያካተተ የፀጥታ ችግሮችን በጋራ የሚያይ መድረክ በማቋቋም ሂደቱ ሰላማዊ እንዲሆን አድርጓል፡፡

**መራጮች ምዝገባ እና የድምፅ ሰጪዎች መረጃ**

የድምፅ ሰጪዎች ሕዝበ ውሳኔው ድምፃቸውን ለመስጠት እንዲመዘገቡ ለመቀስቀስ በሬዲዮና በቴሌቪዥን የተለያዩ የምዝገባ መስፈርቶችን የሚገልጹ እንዲሁም ስለድምፅ አሰጣጡ የሚያብራሩ መልዕክቶች ተላልፈዋል፡፡ በድምፅ ሰጪዎች ምዝገባና ድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ የዜጎች መብት እንዳይገደብ እና የሂደቱን ሰላማዊነት ለማረጋገጥ የሚያግዙ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

ከነዚህም መካከል የመጀመሪያው የቦርዱ አመራር አባላት በሀዋሳ፣ በይርጋአለም፣ በወንዶ ገነት፣ በበሌላ፣ በመዘዋወር የድምፅ ሰጪዎች ምዝገባና ድምፅ ሰጪዎች ድምፅ አሰጣጥ ሂደት ክትትል በማድረግ የታዩ ጉድለቶች እና የአሠራር ዝንፈቶች እንዲስተካከሉ ያደረጉ ሲሆን፣ በተጨማሪም ዜጎች በድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ እንዲሁም በድምፅ መስጠት ሂደቱ የታዘቧቸውን ግድፈቶች በቀጥታ ለቦርዱ ለማሳወቅ እንዲችሉ የቀጥታ የስልክ መስመሮች ተዘጋጅተው ለመገናኛ ብዙሃን እና ማህበራዊ ሚዲያ ይፋ ተደርጓል፡፡

**መራጮች ምዝገባ**

የድምፅ ሰጪዎች ምዝገባው ጥቅምት 27 ቀን 2012 ዓ.ም. እስከ ኅዳር 06 ቀን 2012 ዓ.ም. ድረስ የተከናወነ ሲሆን በአጠቃላይ የተመዘጋቢዎች ቁጥር 2,304,577 ሆኖ ተመዝግቧል። በምዝገባ ሂደቱ ሙሉ ለሙሉ ሰላማዊ በሆነ መልኩ የተከናወነ ሲሆን የዞኑ እና የክልሉ የጸጥታ አካላት፣ የፌደራል ፓሊስ እንዲሁም የመከላከያ ሰራዊት ለሂደቱ ሰላማዊነት ከፍተኛ ትብብር አድርገዋል። የመራጮች ምዝገባ በዞኑ እና በሀዋሳ ከተማ መስተዳድር ለሚኖሩ ማንኛውም ህጋዊ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ዜጎች ክፍት ሆኖ ከጥቅምት 27 እስከ ኅዳር 06 ቀን 2012 ዓ.ም. ድረስ ምዝገባው ተከናውኗል።

**መራጭነት ምዝገባን አስመልክቶ የተወሰዱ ማረምያዎች**

1. የመራጭነት ምዝገባ እና ለመመዝገብ የሚያስፈልገውን ሰነድ አስመልክቶ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች በመነሳታቸው በምርጫና ፓለቲካ ፓርቲዎች አዋጅ 1162/2011 አንቀጽ 21 መሠረት ማንኛውም በዞኑ ለ6 ወራት ኖረና ዕድሜው 18 ዓመት የሞላው ግለሰብ ከሚከተሉት አንዱን በማቅረብ መመዝገብ የሚችል መሆኑን ቦርዱ አሳውቋል።
    - ያልታደሰም ቢሆን ማንነትን የሚያሳይ የቀበሌ ነዋሪነት መታወቂያ፣
    - ማንነትን የሚያሳይ ማንኛውንም ዓይነት ፎቶ ያለበት መታወቂያ (የመሥሪያ ቤት፣ መንጃ ፍቃድ፣ ፓስፓርት… የመሳሰሉት)፣ ሆኖም ይኼ መታወቂያ መኖሪያ አድራሻን ሊያሳይ ካልቻለ ተጨማሪ ሶስት መታወቂያ ያላቸው ምስክሮችን በማስመስከር መመዝገብ ይቻላል፣
    - ምንም ዓይነት መታወቂያ ከሌላው ደግሞ ነዋሪነቱን የሚመሰክሩ ሶስት የነዋሪነት መታወቂያ ያላቸው ምስክሮችን በማምጣት መመዝገብ ይችላል።

በማንኛውም የመራጮች ምዝገባ ሂደት ያልተስማማ አካል ለወረዳ ቅሬታ ሰሚና ለዞን አስተባባሪዎች አቤት የማለት መብቱ የተጠበቀ መሆኑን አሳውቋል።

2. ቦርዱ ሂደቱን በሚመራበት ወቅት የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም የምዝገባ ሂደቱ ሰላማዊ እና የተቀላጠፈ እንዲሆን መረጃዎች በመሰብሰብ የተለያዩ እርማት አድርጓል ከእነዚህም መካከል፦
    - ቦርዱ በደረሰው ሪፓርትና ባደረጋቸው የተለያዩ የመስክ ጉብኝቶች ከተመለከታቸው ክፍተቶች መካከል በምርጫ ጣቢያዎችና በ200 ሜትር ርቀት ውስጥ መገኘት የማይገባቸው ሰዎች እንዲሁም የተከለከሉ ምልክቶች በመታየታቸው እንዲስተካከሉ አድርጓል፣
    - እንዲሁም ማንኛውንም ዓይነት የቀበሌ፣ የወረዳ እና የመንግሥት አስተዳደር ተቋማት ሠራተኞች በምርጫ ጣቢያው ውስጥ መገኘት እንደማይችሉ ለሲዳማ ዞን እና ለሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ቦርዱ አሳውቋል፣
    - ለምርጫ አስፈጻሚዎችም የአፈጻጸም ክፍተት የታየባቸውን ጉዳዮች አስመልክቶ ገለጻ የተደረገላቸው ሲሆን ቦርዱ ከዚህ ቀድሞ እንዳሳወቀው የመራጮች ካርድ ወደ ቤት በመውሰድ ከፍተኛ ጥፋት የተገኘባቸው አንድ አስፈጻሚ ከሥራ ሲሰናበቱ፣ የመራጮች መዝገብን ይዘው ከአካባቢው ለመሰወር የሞከሩ ሌላ አስፈጻሚ በቁጥጥር ሥር ውለው ምርመራ ተደርጓል።

3. የታዛቢዎችን እንቅስቃሴ ሲያውኩ የተገኙ አንድ የከተማው አስተዳደር አባል ባደረሱት ምርጫ ሂደትን የማስተጓጎል ጥፋት በፌደራል የወንጀል ምርመራ እንዲደረግባቸው ተደርጓል።

4. ቦርዱ ባስተዋወቀው ጥያቄ እና ጥቆማ ማቅረቢያ የስልክ መስመር ከቀረቡ ጥቆማዎች መካከል ዋነኛ የሆነውን ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በተለይ መታወቂያን አስመልክቶ የነበረውን የመረጃ እጥረት ለመቅረፍ ለአስፈጻሚዎች የመመዝገቢያ መስፈርቶቹን በድጋሚ እንዲከለስላቸው የተደረገ ሲሆን በተለያዩ የሚዲያ ተቋማት የመመዝገቢያ መስፈርቶች ግልጽ እንዲሆኑ የማስተዋወቅ ሥራዎች ተሰርተዋል። እንዲሁም በተደጋጋሚ አቤቱታ የቀረበባቸው ቀበሌዎችን በአስተባባሪዎች ክትትል እንዲደረግባቸው ተደርጓል።

5. ከአስተዳደር ወሰን ጋር በተያያዘ መካከል አንዱ የሆነው የምዕራብ አርሲ ዞን አዋሳኝ በሆነው በወንዶ ገነት ወረዳ ኤዶ ቀበሌ ምርጫ ጣቢያ ቁጥር 1 ላይ የቀረበ አቤቱታን ቦርዱ ከማህበረሰብ አባላት ጋር በመነጋገር እንዲሁም ከሲዳማ ዞን አመራሮች ጋር በመወያየት ችግሩን ለመፍታት ጥረት አድርጓል፡፡ በዚህም መሠረት በተመሳሳይ ቀበሌ ከሚገኘው ምርጫ ጣቢያ 2 ጋር እንዲዳበል የተደረገ ሲሆን ይህም የሂደቱን ሰላማዊነት ለማስቀጠልና የአስፈጻሚዎችንም ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በዚህ ሂደት ተቋርጦ የነበረው የአንድ ቀን የመራጮች ምዝገባ በኅዳር 07 ቀን 2012 ዓ.ም. እንዲከናወን ተደርጓል፡፡

6. ቦርዱ ከፍተኛ የተመዝጋቢ ቁጥር ያለባቸውን ጣቢያዎች በመለየት የድምፅ መስጫው ቀን ተጨማሪ 175 ጣቢዎችን ቀድሞ ምዝገባ ከተደረገበት ጣቢያ ጎን የሚያቋቁም ሲሆን ይህም የድምፅ መስጠት ሂደቱን የተቀላጠፈ እና በታሰበለት ሰዓት እንዲከናወን ያደርገዋል፡፡

## የሕዝበ ውሳኔው ታዛቢዎች

የሕዝበ ውሳኔውን ሂደት ሰላማዊ፣ ፍትሃዊነት እና ግልጽነቱን ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም ለወደፊት መሻሻል ላለባቸው አሠራሮች ትምህርት ለመውሰድ ለ128 የሲቪል ማህበራት ታዛቢዎች እና 74 የአገር ውስጥና የውጪ ሚዲያ ጋዜጠኞች ሂደቱን እንዲታዘቡና እንዲዘግቡ የሚያስችል እውቅና ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ጋር በመነጋገር የኮሚሽኑ 20 ታዛቢዎች ሕዝበ ውሳኔውን እንዲታዘቡ ተደርጓል፡፡

በኢትዮጵያ መንግሥት ሕዝበ ውሳኔውን እንዲታዘቡ ፍቃድ የተሰጣቸው የአሜሪካን መንግሥት ወኪሎችና ዲፕሎማቶች ሕዝበ ውሳኔን እንዲታዘቡ አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጓል፡፡

## የሕዝበ ውሳኔ የድምፅ መስጫ ቀን

የሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ በታቀደለት መሠረትና በሰላማዊ ሁኔታ የተከናወነ ሲሆን በእለቱ ምርጫው ከጠዋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት የተከናወነ ሲሆን በሰው ብዛት የተነሳ 9 ምርጫ ጣቢያዎች ላይ የድምፅ መስጠት ሂደቱ እስከ ምሽቱ 2 ሰዓት ድረስ ተራዝሟል፡፡

## ሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ ጊዜያዊ ውጤት

በዚህም መሠረት በአጠቃላይ ከተመዘገበው 2,280,147 መራጭ 2,277,063 ሰው ድምጹን ሰጥቷል፡፡ ይህም የምርጫ ቀን የድምፅ መስጠት ተሳትፎ (voter turnout) 99.86% መሆኑን ያሳያል፡፡ ሲዳማ በነባሩ ክልል ውስጥ እንዲደራጅ ጎጆ ምልክትን የመረጠ ሰው ብዛት 33,463 ሲሆን የሲዳማ በክልልነት መደራጀትን ሻፌታን የመረጠ ሰው ብዛት 2,225,249 ነው፡፡ በውጤቱም ሻፌታ የመረጠው 98.51% ሲሆን ጎጆን የመረጠው 1.48% ነው፡፡ በሂደቱ የዋጋ አልባ ድምፅ ቁጥር 18,351 (0.000002%) ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 47/2/ እና /3/ ማንኛውም ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ የራሱ ክልል የመቋቋም መብት አለው በማለት በሚደነግገው መሠረት የሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ ተፈጽሟል፡፡ የዞኑ ነዋሪዎች በነፃ ፈቃዳቸው በሰጡት ውሳኔ መሠረት ሲዳማ ክልል ሆኖ መደራጀት የሚያስችለውን ድምፅም በዚህ ውሳኔ አግኝቷል፡፡

## ሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ የመጨረሻ ውጤት

ቦርዱ ከመጀመሪያ ደረጃው ውጤት በማስከተል የእያንዳንዱን የምርጫ ጣቢያዎች ውጤት በዝርዝር በመገምገም፣ የድምር እንዲሁም ሌሎች የምርጫ ውጤት አለመጣጣም (discrepancies) ያለባቸውን

ጣቢያዎች በማየት በኅዳር 24 ቀን 2012 ዓ.ም. ውሳኔ አስተላልፎ የሚከተለውን የመጨረሻ ውጤት አሳውቋል፡፡

በአጠቃላይ ድምፅ ከተሰጠባቸው 1,692 ምርጫ ጣቢያዎች እና ተጨማሪ 169 ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል በ235 የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ቦርዱ የተለያዩ የድምርና የውጤት አለመጣጣም ችግሮች (discrepancies) አግኝቷል፡፡ እነዚህ ምርጫ ጣቢያዎች ላይ የተገኙት ችግሮች አስፈጻሚዎች ቁጥር በሚደምሩበት ወቅት የተገኘ የቁጥር ድምር ችግር እና ድምፅ የሰጡ መራጮች ድምፅ ከተመዘገቡ መራጮች ድምፅ ከፍተኛ የመሆን ችግሮች ናቸው፡፡

እንዲህ ዓይነት ችግሮች በሚያጋጥሙበት ወቅት የችግሩን ምንጭ ለማወቅ የድጋሚ ቆጠራ መደረግ ቢኖበትም፣ ቦርዱ በአማራጭ ውጤቶቹ መካከል ያለው የውጤት ልዮነት ከፍተኛ ከመሆኑ አንጻር በውጤቱ ላይ ለውጥ ስለማያመጣ፣ በሂደቱ ተአማኒነት ላይ ጥያቄ ስለማያስነሳ እንዲሁም የድጋሚ ቆጠራ በማዘዝ ውጤት ማሳወቂያ ጊዜው መንተት የለበትም በሚል የድጋሚ ቆጠራ ማካሄድን አስፈላጊ ሆኖ አላገኘውም፡፡

በዚህም መሠረት ዓለም አቀፍ የምርጫ ውጤት አስተዳደር ልምድን፣ የምርጫው ዓይነት ሕዝበ ውሳኔ መሆኑን እና በተወሰኑ ጣቢያዎች የተፈጠረው አለመጣጣም በአጠቃላይ የድምፅ ሰጪዎች ድምፅ ላይ የሚያመጣውን ተፅእኖ ውስንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ቦርዱ ችግር ከተገኘባቸው ጣቢያዎችን ሁኔታ አይቶ የሚከተሉትን ውሳኔዎች ሰጥቷል፡፡

1. ከተመዘገበው መራጭ በላይ ድምፅ ተሰጥቶ የተገኘባቸው 127 ምርጫ ጣቢያዎች ላይ ያለ ውጤት እንዲሰረዝ፣

2. በቆጠራ እና በድምር ስሌት ስህተት ከተገኘባቸው ጣቢያዎች መካከል የታየው ልዩነት 10 ድምፅ እና ከዚያ በታች የሆኑ ልዮነቶች ዋጋ እንዳላቸው ድምፅ እንዲቆጠሩ፣ ነገር ግን በ10 ድምፅ በላይ የድምር ልዮነት የተገኘባቸው ጣቢያዎች ውጤት እንዳይካተት ወስኗል፡፡ በዚህም መሠረት 37 ምርጫ ጣቢያዎች በከፍተኛ የድምርና የስሌት ስህተት የተነሳ ውጤታቸው ተሰርዟል፡፡

በአጠቃላይ በማጠናቀቂያ ውጤቱ 164 ምርጫ ጣቢያዎች ላይ ያሉ ውጤቶች ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ምክንያቶች የተነሳ እንዲሰረዙ የተደረገ ሲሆን 71 የምርጫ ጣቢያዎች ግን የድምር ልዮነቱ ከ10 ድምፅ በታች በመሆኑ ስህተት ቢኖራቸውም ውጤታቸው ዋጋ ኖሮት እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

### የውጤት መግለጫ ዝርዝር

የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር - 2,304,577
ድምፅ የሰጡ መራጮች ቁጥር - 2,279,022
በመቶኛ - 98.8911%
ድምፅ ያልሰጡ መራጮች ቁጥር - 25,555
በመቶኛ - 1.10888 %

### አጠቃላይ ውጤት

ዋጋ አልባ ድምፅ መስጫ ወረቀት - 16,624
ለሻፌታ (ለሲዳማ ክልልነት መደራጀት ድምፅ የሰጡ) መራጮች ቁጥር - 1,984,283
በመቶኛ - 97.7%
ለጎጆ (በደቡብ ክልል ለመቆየት ድምፅ የሰጡ) መራጮች ቁጥር 30,018

በመቶኛ - 1.478%
የተሰረዘ ድምፅ - 248,097

የውጤቱ ዝርዝር በዚህ ማየት ይችላሉ፡፡

## በሕዝበ ውሳኔው ሂደት በቦርዱ ተግባራዊ የተደረጉ ማስተካከያዎች

- የአካባቢ ሚሊሻ አባላት የምርጫ ጣቢያዎችን ጸጥታ አጠባበቅ ምንም ዓይነት ሚና እንዳይኖራቸው ተደርጓል፣
- በሕዝበ ውሳኔው አፈጻጸም ያልተገባ ጣልቃ ገብነት የፈጸሙ ሰዎች በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ተደርጓል፣
- በሕዝበ ውሳኔው መራጮች ምዝገባ እና ድምፅ መስጠት ሂደት ሁለቱም አማራጮችን የሚወክሉ ወኪሎች እንዲገኙ ጥረት ተደርጓል፣
- የተጓደሉ የሕዝበ ውሳኔ ማስፈጸሚያ ቁሳቁሶች በፍጥነት እንዲሟሉ ተደርጓል፡፡

## ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

የሕዝበ ውሳኔው አፈፃፀም ሰላማዊና ህጋዊ መሆኑ በዚህ ሂደት የተገኘ በጎ ውጤት ሲሆን፣ ለዝግጅት ከነበረው አጭር ጊዜም አንጻር የቦርዱ አፈጻጸም የተሳካ ነው ብሎ ያምናል፡፡ የአፈፃፀም ሂደቱ ጠቃሚ ትምህርት የተገኘበት መሆኑን ያህል ተግዳሮቶች የነበሩበት በመሆኑ ለቀጣይ ትምህርት ይሆን ዘንድ የሚከተሉትን ማንሳት ተገቢ ይሆናል፦

- የህግ ማዕቀፍ እንዲወጣ (የአነስተኛ ቡድኖች መብት ጥበቃ፤ የሀብት ክፍፍል) በቦርዱ የቀረበው ጥያቄ በክልሉ ምክር ቤት የተሰጠው ምላሽ መዘግየት፣
- የሕዝበ ውሳኔው ቅስቀሳ ሂደት የአንድን ወገን አማራጭ ብቻ የቀረበበት መሆኑ እና የሕዝበ ውሳኔውን ሂደት እንዲታዘቡ የክልሉ መንግሥት ወኪሎች እንዲመድብ በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብለትም አለመመደቡ፣
- የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን ለመወሰን የሚያስፈልገው የሕዝብ ቁጥር የተሟላ መረጃ አለመኖር፣
- በተወሰኑ የሀዋሳ ከተማን የገጠር አካባቢ ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የማይመለከታቸው ሰዎች መገኘት፣ በድምፅ ሰጪዎች ላይ በአንዳንድ ጣቢያዎች ተፅእኖ የማሳደር ሁኔታ መታየት፣
- በአንዳንድ ቦታዎች በድምፅ ሰጪዎች ብዛት ምክንያት የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መጨናነቅ መከሰቱ፣
- በሕዝበ ውሳኔው ውጤት አገላለጽ ላይ ከሀዋሳ ከተማና ከዞኑ መስተዳድ ተቋማት ኃላፊዎች በቦርዱ ይፋዊ መግለጫ ከመሰጠቱ በፊት አስቀድሞ የመመገመት (Projection) እና የመግለጽ ችግር መታየቱ፣
- በአንዳንድ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በህግ የተቀመጠን የምርጫ ጣቢያ መክፈቻ እና መዝጊያ ሰዓት አለመጠበቅ እንደዋና ተግዳሮት የሚጠቀሱ ሲሆን ማለትም የክልሉ የጸጥታ ተቋማት፣ የደቡብ እዝ የአገር መከላከያ ሰራዊት የሕዝበ ውሳኔ ቁሳቁስ ማጓጓዝ፣ የአካባቢ ጸጥታ እና ደህንነትን በመጠበቅ፣ የአስፈጻሚዎች ስምሪትን እንዲሁም ድምፅ የተሰጠባቸውን ሰነዶችን ጥበቃ በማድረግ እጅግ የሚመሰገን ድጋፍ ማድረጋቸው እና በሕዝበ ውሳኔው ሂደት ከፍተኛ ቅንጅት መኖሩ እንደትልቅ ስኬት የሚነሳ ነው፡፡

ከሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ ጋር የተያያዙ መግለጫዎች ከስር ማውረድ ይችላሉ፡፡